# የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት

# THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA

HIS IMPERIAL HIGHNESS PRINCE ERMIAS SAHLE-SELASSIE HAILE-SELASSIE
PRESIDENT

የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት የፖፕ ፍራንሲስ ዕረፍትን አስመልክቶ ለሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንና በመላው ዓለም ለሚገኙ የእምነቱ ተከታዮች በሙሉ፤ በተለይም በሀገረ ኢትዮጵያ ለሚገኙ ምዕመናን የተሰማውን ጥልቅ ሐዘን ገልጧል። የፖፕ ፍራንሲስ ውርሰ አሻራ የሆኑትን ሰላምና ፍቅር የሚዘክረውን መግለጫ ያወጡት የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት ፕሬዚደንት ልዑል ኤርሚያስ ሳህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ ናቸው።

በመግለጫቸው “በወርኃ ግንቦት ፳፻፲፫ ዓም ብፁዕ ወቅዱስ ፖፕ ፍራንሲስ ጋር ለመገናኘት መልካም ዕድል ገጥሞኝ ነበር" ያሉት የዘውድ ምክር ቤቱ ፕሬዚደንት “ፖፕ ፍራንሲስ ወደ ሰላም የሚያመራ ርሕራሔንና ድፍረትን የተላበሰ ተግባርን አዋድደዋል። ተልዕኳቸው በእኛ ግብር፣ በእኛ አገልግሎት፣ በእኛ ዕሴቶቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥና በመላው ዓለም በማራመድ ውሳኔ ሕያው ሆኖ ይኖራል” ሲሉ የፖፕ ፍራንሲስን ውርሰ አሻራዎችን የማስቀጠል ኃላፊነት የሁሉም ሰብዓዊያን ድርሻ መሆኑን አበክረው አሳስበዋል።

ከአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ በኢትዮጵያና ቫቲካን ያለው ግንኙነት ምዕተ ዓመታትን ያስቆጠረ መሆኑን ያስታወሰው መግለጫ፤ አያታቸው ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በወርኀ ኅዳር ፲፱፻፷፫ ዓም ከፖፕ ጳውሎስ ፮ኛ ጋር እንደተገናኙ በማስታወስ ልዑል ኤርሚያስም በ፳፻፲፫ ዓም ከፖፕ ፍራንሲስ ጋር መገናኘታቸው ታሪካዊ አጋጣሚ መሆኑን አመልክተዋል። የታሪካዊ ግንኙነቱን መታደስ በማስመልከትም ከፖፕ ፍራንሲስ ጋር በተገኛኙበት ወቅት የፓፓል ኢትዮጵያውያን ኮሌጅን በመጎብኘታቸው ልዑል ኤርሚያስ "ክብር ተሰምቶኛል" ያሉ ሲሆን፤ "የፖፕ ፍራንሲስን ካለፉት ትውስታዎቻችን ይልቅ የወደፊት የጋራ ዕድሎቻችን ላይ እናተኩር" በሚል ዕሳቤ በውል የሚረዱ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ልዑል ኤርሚያስ፤ የፖፕ ፍራንሲስን የአፍሪካ ቀንድ የሰላምና ዕርቅ ፍለጋ ግላዊ ሚና እንደሚረዱና ለደቡብ ሱዳን ሰላምና መረጋጋት ልባዊ ፀሎት ማድረግ አንስተው “በ፳፻፲፪ ቅዱስነታቸው ተንበርክከው የደቡብ ሱዳን ፕሬዚደንት ሳልቫ ኪር እና ምክትል ፕሬዚደንት ሪክ ማቻርን እግር የሳሙበትን ወቅት አንረሳም፤ የ፳፻፲፫ ዓም ግንኙነታችንን ተከትሎም ለኢትዮያ እንደፀለዩ እናውቃለን" ብለዋል።

"የኢትዮጵያ መንፈሳዊና ምድራዊ መሪዎች የፖፕ ፍራንሲስን ምሳሌ ተከትለው ለሀገራችን ሰላም እንዲፀልዩና እንዲሠሩ እናሳስባለን" ሲሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

Amharic Translation courtesy of Mr. Kassahun Negewo of SBS Australia Radio Amharic Service.